# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ........................................................................................i
ክፍል አንድ ..................................................................................1
መግቢያ......................................................................................1
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አመሰራረት ....................................................1
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራእይ እና ተልዕኮ..................................................3
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር.............................................3
የመ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ....................................................4
**የሰው ኃይል** ..............................................................................5
የፋይናንስ ምንጭ...........................................................................5
የኦዲቱ ዓላማ ...............................................................................5
ለኦዲት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ...................................................6
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች..................................6
**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች** ..........................................................6
**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት** .............................................................6
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ......................................................................7
የቱሪዝም አስጎብኚ ድርጅት የማስጎብኚት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ.........................8
/ Process Description/.....................................................................8
ክፍል ሁለት ..................................................................................9
የኦዲት ግኝቶች ..............................................................................9
2.1 የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እና የድርጅቶቹ አገልግሎት አሰጣጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤............9
ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ አሰጣጥን ማውጣቱን በተመለከተ .......................................................................9

በቱሪስት አስጎብኚነት ለሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን በተመለከተ፣ ........................................................................................10

የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች መለያ ዓርማ መጠቀማቸውን በተመለከተ ........................................................11

የአስጎብኚዎች መመሪያ /Tour Operators Guide/ መዘጋጀቱ እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........................................................................12

አስጎብኚ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውን በተመለከተ...................................................................13

የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያግዝ የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ .................................................14

በአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ..........................................................................15

በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ የላቀ አገልግሎትና ብቃት ያሳዩ አካላት የሚበረታቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ ......................................................16

2.2 ለአስጎብኚ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ጥራት ...........................17

ያለው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በተመለከተ፤..............................................17

ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ የገቡ ተሽከርካሪዎች መረጃ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መያዙን በተመለከተ ........................................................................................17

አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ንብረቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ለማስጎብኘት አገልግሎት ስለማዋላቸው ..................................................18

2.3 የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶችን በሚመለከት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር፣ የመረጃ ልውውጥና አያያዝን ቀልጣፋ መሆኑን በተመለከተ፡፡.........................................................................................19

የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት ስለመዘርጋቱና እንዲሻሻል ስለመደረጉ.....19

የቱሪዝም የገበያ ትስስር መፍጠርን በተመለከተ ..........................................20

አገሪቱ ያላትን የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁና እንዲለሙ መደረጉን በተመለከተ ........................................................................21

የማስጎብኘት አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መኖሩን በተመለከተ ......22
ክፍል ሶስት ......24
መደምደሚያ ......24
ክፍል አራት ......26
የማሻሻያ ሃሳቦች ......26
አባሪ 1፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ......29
አባሪ 2፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ......30
አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው እና ማስረጃ የተሰበሰበባቸው ባለድርሻ አካላትና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ዝርዝር ......33

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቱሪዝም በዓለም ላይ ፈጣን ዕድገትን እያስመዘገቡ ካሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ አገራዊ ልማትን በመደገፍና በማፋጠን ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ቱሪዝም በውጭ ምንዛሪ ምንጭነት፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ የምርትና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በማስፋፋት፣ የሥራ ስምሪት ዕድልን በመፍጠርና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

2. ኢትዮጵያ ቱሪዝምን በዘላቂነት ለማልማት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተፈጥሮዓዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች ባለቤት ናት፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የቱሪዝም ልማት ፕላን ተዘጋጅቶ ከወጣበት ከ1958 ዓ.ም ወዲህ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ተቋማት በዓይነትና በአገልግሎት ጥራት ደረጃ እድገት እያስመዘገቡ የሚያበረክቱትም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ከጊዜ ወደ ጊዜ አዎንታዊ ለውጥ በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ ይህን መልካም ጅምር በማጠናከር ከቱሪዝም ልማት ህዝብን በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ በዘርፉ የተሰማሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ሁሉ በጋራ በመንቀሳቀስ የታሰበው ዕድገትና ለውጥ በተፈለገው መጠንና ፍጥነት እንዲመጣ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3. ሀገሪቱ ከቱሪዝም ዘርፍ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ለማግኘት እንዲቻል የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ሚና ጉልህ ድርሻ ስላለው አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ወሳኝ ነው፡፡

## የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አመሰራረት

4. በ1954 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የቱሪዝም ሥራ በኢትዮጵያ የተፀነሰው በአንድ በጎ አሳቢ የቱሪዝም ሥራ ባለሙያ/Initiator/ አማካኝነት ነበር፡፡ የቱሪዝም ሥራው በቢሮ ደረጃ ሲደራጅ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንድ ቢሮ ተሰጥቶት ከቆየ በኋላ እንደገና ሌላ ቢሮ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦሌ ኤርፖርት ውስጥ ተቀምጦ ከውጭ ሀገር የሚመጡትን የውጭ ሀገር ዜጎች አገራችንን በማስተዋወቅ ሥራውን ጀመረ፡፡ ከዚያም ህጋዊ ሰውነት ኖሮት ሥራውን በራስ አቅም እንዲመራ በ1957 ዓ.ም. በዘመኑ ከነበረው የጽህፈት ሚኒስቴር በተላለፈው ሰርኩላር ትዕዛዝ ቁጥር 36/57 መሰረት የኢትዮጵያ

ቱሪስት ድርጅት በሚል ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቋቋመ፡፡ ድርጅቱ በተቋቋመበት ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የበላይ ጠባቂነት ራሱን ችሎ እንዲተዳደር የተወሰነ ሲሆን፣ የተቋቋመበት ዓላማም ቱሪስቶች አገራችንን በብዛት እንዲጎበኙ ለማስቻል በማሰብ ነበር፡፡

5. የተሰጡትም ኃላፊነቶች አገሪቱ ከዘርፉ ከፍ ያለ ጥቅም እንድታገኝ ለማስቻል፣ የቱሪዝም ሥራዎችን ለማስፋፋት፣ አስፈላጊ የሆኑ ድርጅቶች የሚቋቋሙበትን ስልት ለማመቻቸት፣ የሀገር ውስጥ የሕዝብ ለሕዝብ ትውውቅ ባህል እንዲጎለብት እና የአገሪቱን መልካም ዝናና ገፅታ ለማስተዋወቅ የሚያግዙ የሕትመት መረጃዎችን እያሳተመ እንዲያሰራጭ ነበር፡፡

6. በ1958 ዓ.ም. በጽሕፈት ሚኒስትሩ ትዕዛዝ ቁጥር 46/1958 ድርጅቱ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋር ተቀላቅሎ የማስታወቂያና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲደራጅ ተደረገ፡፡ በ1961 ዓ.ም. በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 371/1961 ዓ.ም. መሠረት ማሻሻያው የኢትየጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅትንና የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን ጨምሮ በሥሩ በማዋቀር እንዲያስተዳድር ተደረገ፡፡

7. በ1963 ዓ.ም. በወጣው የመንግስት ማስታወቂያ ቁጥር 412/1963 ዓ.ም. መሠረት በተደረገው የአደረጃጀት ለውጥ የኢትዮጵያ ቱሪስት ድርጅት ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተቀላቅሎ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲደራጅ ተደረገ፡፡ በ1967 ዓ.ም. በተደረገው የአደረጃጀት ማሻሻያም በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር በ21/1967 መሠረት የኢትዮጵያ ሆቴሎችና ቱሪዝም ድርጅት በሚል ስያሜ እንዲተዳደር ተደረገ፡፡ በ1969 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁጥር 127/69 መሠረት በተደረገው አዲስ አደረጃጀት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለብቻው እንዲደራጅ፣ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ከንግድ ሚኒስቴር ተዋህዶ ንግድና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲደራጅ ተደረገ፡፡ በ1972 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁጥር 182/72 መሠረት በተፈጠረው አዲስ አደረጃጀት የኢትዮጵያ ቱሪዝምን ሥልጣንና ተግባር ሰፋ በማድረግ በኮሚሽን ደረጃ ራሱን ችሎ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን በሚል ስያሜ ተደራጀ፡፡ እንዲሁም በ1987 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 11/87 መሠረት እንደገና በኮሚሽን ደረጃ እንዲቋቋም ተደርጎ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን በሚል ስያሜ ሲሠራበት ቆይቷል፣

8. በ1998 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 471/1998 መሠረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባደረገው አዲስ አደረጃጀት ባህል ከኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን ጋር ተዋህዶ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተብሎ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በ2003 ዓ.ም. የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 916/2008 እንደተሻሻለ) መሠረት ተቋቋመ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራእይ እና ተልዕኮ

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

9. ኢትዩጵያ በ2017 ዓ.ም ባህላዊ ሀብቶቿና የተፈጥሮ መስህቦቿ ለምተው በቱሪዝም መዳረሻነት ከመጀመሪያዎቹ 5 የአፍሪካ አገራት አንዱ እንድትሆን ማድረግ፡፡

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልእኮ

10. የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሐረሰቦችና ሕዝቦች ባህላዊ ሃብቶችና ተፈጥሮአዊ የቱሪስት መስህቦች በህብረተሰቡና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በማጥናት፣ በማልማት፣ በማስተዋወቅ እና የአገሪቷን መልካም ገጽታ በመገንባት ዘላቂ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ፡፡

## የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 916/2008 እንደተሻሻለ) መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፣

- የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች እና መልካም ገጽታ በአለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፤ የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ያበረታታል፤
- የሀገሪቱ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የየአካባቢው ማህበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቻል፤

- የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በአግባቡ መመራቱን ያረጋግጣል፤
- የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤
- በቱሪዝም የሰመረ አገልግሎት እንዲኖርና የቱሪስቶችም ደህንነት እንዲረጋገጥ የሚያስፈልገው የብዙ ወገኖች የሥራ ቅንጅት እውን እንዲሆን ለሚፈጠሩ የጋራ የምክክር መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፤
- በሰው ሀይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካይነት የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤
- የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ፣ ባህላዊ ቅርሶችና እሴቶች እንዲጠኑና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
- የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋዎች እንዲጠኑና፣ ሥነ ፅሁፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባሮች ያከናውናል፤
- የባህል ዘርፉ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- የባህል ዘርፉ የህዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሰረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- የኪነ-ጥበብ እና ሥነ-ጥበብ የፈጠራ ችሎታዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- የሀገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበት አግባብ ያመቻቻል፤
- የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናክራል፣ ያሰራጫል፤

## የመ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው የተቋሙ የበላይ አመራር በሆኑ በአንድ ሚኒስትር እና ሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች

ምክር ቤት ነው፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአራት ዋና ዋና የሥራ ሂደቶች (Core processes) እና ሰባት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች /Support Processes/ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ **በአባሪ** (1) ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

13. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር 428 ቋሚ ሠራተኞች በመዋቅር የጸደቀለት ሲሆን እስከ ታህሳስ ወር 2008 ዓ.ም ድረስ 303 ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ፕሮፌሽናል የሆኑ ወንድ 87 ሴት 67 ድምር 154 እንዲሁም ፕሮፌሽናል ያልሆኑ ወንድ 64 ሴት 85 በድምሩ 149 በጠቅላላ ወንድ 151 እና ሴት 152 በድምር 303 ሰራተኞች አሉት፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

14. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2005 እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | ተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2005 | 39,434,600.00 | 38,792,441.42 | (98.37%) |
| 2006 | 55,410,877.85 | 54,487,594.07 | (98.33%) |
| 2007 | 57,452,950.00 | 55,970,573.9 | (97.42%) |

## የኦዲቱ ዓላማ

15. የኦዲቱ ዓላማ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## ለኦዲት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ **"የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን መገምገም"** መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

17. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም:-

1. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እና የድርጅቶቹ አገልግሎት አሰጣጣቸው ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. ለአስጎብኚ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ጥራት ያለው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በተመለከተ ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር፣ የመረጃ ልውውጥና አያያዝን ቀልጣፋ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

18. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመመዘን የሚረዱ 28 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጅክ ዕቅድ፣ ለአስጎብኚ ድርጅቶች የወጡ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች፣ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች መልካም የሥራ ተሞክሮ እና የመረጃ ድህረ ገጾች /web site/ ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ **በአባሪ 2** ተያይዘዋል፡፡


## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

19. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2005 እስከ 2008 የመጀመሪያው ሩብ በጀት አመት ያሉትን ሶስት አመት ከሶስት ወራት የሥራ ክንውኖች ነው፡፡

20. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሲሆን በተጨማሪም በናሙና የተመረጡ አሥራ አምስት የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር እና ዋና ባለድርሻ አካላት የሆኑትን ኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ አዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እና አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ የሚያመለክቱ ተያያዥ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስ እና በናሙና የተመረጡ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሥራ እንቅስቃሴ በአካል በማየት ነው፡፡ በኦዲቱ ወቅት የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

## የቱሪዝም አስጎብኚ ድርጅት የማስጎብኚት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ

## / Process Description/



# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እና የድርጅቶቹ አገልግሎት አሰጣጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

**ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ አሰጣጥን ማውጣቱን በተመለከተ**

21. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል ደረጃ ሊያወጣ እና ባወጣው ደረጃ መሰረትም ተግባራዊ ሊያደርግ እና ስለመደረጉ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

22. ይሁን እንጂ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል እንዲሁም ቱሪስቶች እንደፍላጎታቸው መገልገል እንዲችሉ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ እንዳልወጣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ቢወጣ ከአገልግሎት አስጣጥ አንፃር ቱሪስቶች የተሻለ አገልግሎት የሚሰጡትን ድርጅቶች በቀላሉ በተሰጣቸው ደረጃ በመለየት መገልገል እንዲችሉ እና አመቺ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ለማስፈን እንዲሁም ዝቅተኛ ደረጃ የተሰጣቸው ድርጅቶች የተሻለ ደረጃ ለማግኘት እንዲተጉ እንደሚያግዝ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

23. ስለሁኔታው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለፉት የሥራ ዘመናት በተለይም በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ዕቅዱ ከተገበራቸው አንኳር ሥራዎች አንዱ የነበረው የሆቴሎችን ደረጃ ማውጣትና መመደብ እንደነበር እና ይሄ ሥራ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች የተካሄደና በመሰራት ላይም ያለ መሆኑን፣ በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን በመጀመሪያዎቹ የስራ ዓመታት የአስጎብኚ ድርጅቶችን የደረጃ መስፈርት ማውጣትና ደረጃውን መመደብ የሚያስችል በዕቅድ ተይዞ የዝጅግት ምዕራፍ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን እንዲሁም በቀጣይ የዋናው መስፈርት ዝግጅት ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንደሚከናወን በተላከላቸው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

24. ለቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ባለመውጣቱ ቱሪስቶች የሚፈልጉትን አገልግሎት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ እንዳያገኙ፣ የተሻለ አገልግሎት የሚሰጡትን ድርጅቶች የተሻለ ደረጃ እንዳይኖራቸው፣ አመቺ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዳይሰፍን፣ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው ድርጅቶች የተሻለ ደረጃ ለማግኘት እንዳይተጉ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንዳታገኝ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## በቱሪስት አስጎብኚነት ለሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን በተመለከተ፣

25. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአስጎብኚነት የሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት አውጥቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና የባለሙያዎቹንም የሙያ ብቃታቸውንም በየጊዜው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

26. በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአስጎብኚነት ለሚሰማሩ ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት አዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው አስጎብኚ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች እና ያላቸውን የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግቢ በአካል ቀርበው እንዲታዩ በማድረግ ሲሆን ድርጅቶቹ ያቀረቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ትክክለኛነት (ለምሳሌ፡ የሚፈለጉት ባለሙያዎች በእርግጥ እንዳሉ፣ የድርጅቶቹ የቢሮ ሁኔታ፣ የቢሮ ቁሳቁሶች፣ ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔት፣ ለማስጎብኘት አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ የመስክ ቁሳቁሶች የመሳሰሉት ስለመሟላታቸው) ድርጅቶቹ ባሉበት በአካል በመሄድ እንደማይረጋገጥ እንዲሁም የባለሙያዎቹ የሙያ ብቃት በየጊዜው እንደማይረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. ስለሁኔታው በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርት አውጥቶ በየዓመቱ ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ ቢሆንም የወጣው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ድርጅቶቹ ያላቸውን ንብረቶች እና ተሽከርካሪዎች እንጂ ከማስጎብኘት አንጻር ቱሪስቶች በከፈሉት መጠን አርኪ አገልግሎት ስለማግኘታቸው፣ በድርጅቶቹ ላይ የሚታየው የእድገት ለውጥ እና ለቱሪዝም ዘርፉ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ለመለካት የሚያስችል ካለመሆኑም በተጨማሪ እንደ መስፈርት የተቀመጡት እና አስጎብኚ ድርጅቶቹ በጽሁፍ ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል እንደማያረጋግጥ ገልጸዋል፡፡

28. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በፈቃድ አሰጣጡ ወቅት የነበሩ የአገልግሎት ግብዓቶች ፈቃድ ከተሰጠም በኋላ ስለመኖራቸው ቀደም ባለው ጊዜ ክትትል ይደረግ እንደነበር ገልጸው ከጊዜ በኋላ የአስጎብኚ ድርጅቶች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ የባለሙያዎች እጥረት እያጋጠመ በመምጣቱ የሱፐርቪዥኑ ስራ መቋረጡን፣ በአካል ምልከታ የማረጋገጥ ሥራው እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለበትን የባለሙያ እጥረት ለማስወገድ የመዋቅር ማስፋፊያ ጥናት የተጀመረ ስለሆነ እንደ ፀደቀ ችግሩ እንደሚፈታ መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

29. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት የ በወጣው የመመዘኛ መስፈርት በትክክል የድርጅቶቹን ብቃት አለመረጋገጡ አመቺ እና ጥራት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዳይሰፍን፣ ዝቅተኛ አገልግሎት የሚሰጡት ድርጅቶች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እንዳያደርጉ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንዳታገኝ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች መለያ ዓርማ መጠቀማቸውን በተመለከተ

30. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች የየድርጅቶቹን አርማ በመኪናዎቹ ጎንና ጎን ሊለጥፉ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፈው ዓርማ መጠንን በተመለከተ ስታንደርድ ሊያወጣላቸው እና በሁሉም በማስጎብኘት ሥራ በተሰማሩ ተሽከርካሪዎች ላይ የብቃት ማረጋገጫ ምልክት (ቦሎ)ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

31. ነገር ግን የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች በጎን እና በጎናቸው የሚለጥፉት የየድርጅቶቹን ዓርማ መጠንን በተመለከተ ስታንደርድ እንዳላወጣ እና ድርጅቶቹም ዓርማቸውን ለማስጎብኘት በሚጠቀሟቸው ተሽከርካሪዎች ላይ መለጠፋቸውንና አለመስራተቸውን እንደማይከታተል በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር የቱሪስት ተሽከሪካሪዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ አርማ የሚዘጋጀው በድርጅቶቹ ሲሆን ድርጅቶቹ በራሳቸው በሚፈልጉት ዓይነትና መጠን ቱሪስቶች ከሌሎች ድርጅቶች እንዲለዩዋቸው በማድረግ የሚያሰሩት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

32. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የቱሪስት አስጎብኚ አገልግሎቶች በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ የአስጎብኚ ድርጅቶቹን ስምና አርማ በተሽከርካሪዎቻቸው በግራና በቀኝ በኩል የሚለጥፉ ሲሆን፣ ለማስጎብኘት ሥራ ተሽከርካሪው የተፈቀደለት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ (የቦሎ) አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ተሽከርካሪዎቹ በስራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙበት ወቅት በብቃት ማረጋገጫው መሰረት እየሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥራ እየተከናወነ እንዳልሆነ፣ ወደፊት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራፊክ ፖሊስና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር የቁጥጥሩን ሥራ በጋራ ማከናወን የሚያስችሉ የአሰራር ሥርዓቶች በመቅረፅ ተግባራዊ እንደሚያደርግ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

33. የቱሪስት ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሟቸው አርማዎች መጠን አንድ ወጥ ደረጃ የወጣለት አለመሆኑ፣ ድርጅቱም የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ቦሎ በቀላሉ መለየት የሚያስችል አለመሆኑ፣ ለቱሪስት አገልግሎት የተመደቡ ተሽከርካሪዎችን ቱሪስቶችም ሆኑ ህብረተሰቡ በቀላሉ እንዲለዩዋቸው የማያስችል የሚያደርግ እና በተለይ መንግስት ዘርፉን ለማበረታታት ሲል የፈቀደውን በቀረጥ-ነጻ የገቡትን የቱሪስት ተሽከርካሪዎች ከታለመለት ዓላማ ውጭ አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ማድረግን አዳጋች አድርጎታል፡፡

### የአስጎብኚዎች መመሪያ /Tour Operators Guide/ መዘጋጀቱ እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

34. የአስጎብኚ ድርጅቶች እና አስጎብኚዎቻቸው የሚጠቀሙበት እንዲሁም የየራሳቸውን የአስጎብኚ መመሪያ ለማዘጋጀት እንደ መነሻ የሚያገለግል /minimum standard/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አዘጋጅቶ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ በወጣው መመሪያ መነሻ /minimum standard/ መሰረትም አስጎብኚ ድርጅቶች የራሳቸውን የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ አዘጋጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደ መነሻ የሚያገለግል /minimum standard/ የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ በማዘጋጀት ለአስጎብኚ ድርጅቶች እንዳላሰራጨ እና ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል እንዳላደረገ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ሚኒስቴር

መ/ቤቱ እንደመነሻ የሚያገለግላቸው የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ እንዳልተዘጋጀና፣ ድርጅቶቹም በራሳቸው የአስጎብኚ መመሪያ እንዳላዘጋጁ ገልጸዋል፡፡

36. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው የአስጎብኚ ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት በሚኒስቴር መ/ቤት ተዘጋጅቶ እየተሰራበት እንደሚገኝና መስፈርቱ የወቅቱን የሀገሪቱን እና የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ እያገናዘበ በየወቅቱ መዳበር እንዳለበት የሚታመን ሲሆን ለወደፊቱ እንደሁኔታው ተሻሽሎ እንደሚዘጋጅ እና አስጎብኚ ድርጅቶች በራሳቸው ለሚያዘጋጇቸው የውስጥ አሰራር ማኑዋሎች በጠየቁት ጊዜ የምክር አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን ወደፊትም የውስጥ አሰራራቸው የሚፈተሽበትና እገዛ የሚደረግለት የአሰራር ስርዓት እንደሚዘረጋ ገልጸዋል፡፡

37. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ ተጠቀሰውን መልስ ቢሰጥም የአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት እንጂ አገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት በሚኒስቴር መ/ቤት ተዘጋጅቶ እየተሰራበት እንደማይገኝ እንዲሁም አስጎብኚ ድርጅቶች በራሳቸው ለሚያዘጋጇቸው የውስጥ አሰራር ማኑዋሎች በጠየቋቸው ጊዜ የምክር አገልግሎት እንደማይሰጥ ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ በመቻሉ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

38. እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚ መመሪያ /Minimum Standard Tour Operators Guide/ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ባለማሰራጨቱ እንዲሁም ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ባለመደረጉ በማስጎብኘት አገልግሎት የሚሰማሩ አካላት የአገልገሎቱ ዝርዝር ተግባራት በትክክል አውቀው እንዳይንቀሳቀሱ ሊያደርግ እና ለስነ ምግባር ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## አስጎብኚ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውን በተመለከተ

39. የአስጎብኚ ድርጅቶች በውጭ ምንዛሪ ደንበኞቻቸውን ለማስተናገድ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሊያወጡ ይገባል፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውን እና በየአመቱ ማሳደሳቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ አስጎብኚ ድርጅቶችም ወርሃዊ የቱሪስት ፍሰትን አስመልክቶ የስራ አፈጻጸም እና በውጭ ምንዛሪ ያገኙትን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ሪፖርት በየወሩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲያድስ የውጭ ምንዛሪ እንዲያንቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ስለመኖሩ እና ስለማሳደሳቸው የማያረጋገጥ መሆኑን እና በድርጅቶቹ ሪፖርት የሚደረገው የውጭ ምንዛሪ መጠን ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደማይረጋገጥ ታውቋል፡፡ በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር በውጭ ምንዛሪ እና በብር ያገኙትን ገቢ በየዓመቱ ፈቃድ በሚያድሱበት ወቅት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደሚያደርጉ ነገር ግን ያስገቡትን ገቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትክክለኛነቱን አጣርቶ ሳይሆን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት መስፈርት ስለሆነ ብቻ በመሆኑን ገልጸዋል፡፡

41. ስለሁኔታው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ያመኑበትን የገቢ መጠን በሪፖርት መልክ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቁ ቢሆንም አስገባን ያሉት የውጭ ምንዛሪ መጠን ትክክለኛነት የማረጋገጡ ስራ ያልተሰራ ቢሆንም ለወደፊቱ የክትትልና የቁጥጥር አሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ቁጥጥር እንደሚደረግበት እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ሲያደርጉ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁበት አግባብ እንደምኖር በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

42. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ የውጭ ምንዛሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘታቸውንና በየአመቱ ማሳደሳቸውን፣ እንዲሁም ድርጅቶቹ ያቀረቡት ሪፖርት ያገኙትን ትክክለኛ ውጭ ምንዛሪ የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ስለመሆኑ አለመረጋገጡ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች ካገኙት ትርፍ ለመንግስት መክፈል የሚገባቸውን ትክክኛ ግብር መጠን ከማሳጣቱም በተጨማሪ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ለህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዲጋለጥ በር ይከፍታል፡፡

## የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያግዝ የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

43. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል የድጋፍ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

44. ይሁን እንጂ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል የድጋፍ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እንዳላደረገ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በናሙና የታዩ አስጎብኚ ድርጅቶች እና አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር

ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ስርትፍኬት ከመስጠት፣ የአለም ቱሪዝም ቀን ከማክበር እና ከአስጎብኚ ድርጅቶች በተጠየቀ ጊዜ የድጋፍ ደብዳቤዎችን ከመጻፍ በስተቀር፡ ማህበሩ ከነበረበት ቢሮ እንዲወጣና በራሱ ተከራይቶ እንዲሰራ መደረጉ፣ የስልጠና እና ሌሎች ድጋፎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመደረጉን የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ የሚደረግ የድጋፍ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እንዳልተደረገ እንደማሳያ ሊጠቀስ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

45. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ለቱሪዝም አስጎብኚ ድርጅቶች አቅሙ በፈቀደው መጠን የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝ እና ማህበራቱ ሲጠቀሙበት የነበረውን ቢሮ መንግስት ለሌላ መንግስታዊ ስራ ያዋለው በመሆኑ ማህበራቱ ቢሮ እንዲያገኙ ለኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ደብዳቤ በመጻፍና በመከታተልም ድጋፍ እያደረገ መሆኑንና ይህንንም ድጋፉን ወደፊትም አጠናክሮ እንደሚቀጥል በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ያላቸውን አስተያየት ገልጸዋል፡፡

46. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ ተጠቀሰውን መልስ ቢሰጥም ለአስጎብኚ ድርጅቶች መንግስት የፈቀደው የቀረጥ ነጻ ድጋፍ ካልሆነ በስተቀር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረጉ ድጋፎች እንደሌሉ ከአስጎብኚ ድርጅቶች እና ከድርጅቶቹ ማህበር ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማወቅ በመቻሉ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

47. የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ የሚደረግ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በሚፈልጉት ጊዜ በተፈለገው መጠን ማግኘት እንዳይችሉ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## በአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

48. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

49. ይሁን እንጂ ከአስጎብኚ ድርጅቶች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች በሚገኙባቸው በክልሎች አካባቢ በቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ

ቅሬታዎች (ለምሳሌ፡ ክልሎች በጥቃቅንና አነስተኛ ያቋቋሟቸው ሎካል ጋይድ ያለአግባብ በየጊዜው ዋጋ መጨመር፣ ያላቸው የማስጎብኘት ብቃት አናሳ መሆን፣ ዩኒፎርም አለመኖር፣ ንፅህናን አለመጠበቅ፣ በሆቴሎች አካባቢ ለቱሪስቶች አልጋ ከተያዘ በኋላ ለሌላ ሰው ማከራየት፣ ዋጋ መጨመር፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚደርስባቸው እንግልት እና ወከባ) በአግባቡ መልስ ማግኘት አለመቻል የመሳሰሉት ችግሮች መኖራቸው ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን ማሳያዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

50. ስለጉዳዩ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በየክልሎች ከማስጎብኘት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱና ሌሎች ችግሮች እንዳሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚያውቃቸውና እነዚህንም ተያያዥ በሀገር አቀፍ ትኩረት ተሰጥቶ ሀገራዊ የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 294/2005 እንደተቋቋመ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ የየክልል የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤቶች እስከ ወረዳዎች ድረስ እንዲቋቋሙ መደረጉን እና በመዳረሻዎች አከባቢ ወጥነት ያለው አሰራር መዘርጋት እንዲቻል ሀገራዊ ጥናት ስለተካሄደ ወጥ መረጃዎች እየተዘጋጁ እንደሚገኙ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

51. ከአስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ጥራት ያለው አገልግሎት እንዳይሰጡ እና እንዳይበረታቱ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ መጠን እንዳታገኝ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ የላቀ አገልግሎትና ብቃት ያሳዩ አካላት የሚበረታቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ

52. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት ማበረታቻ ሥርዓት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት ማበረታቻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አስጎብኚ ድርጅቶች ማበረታቻ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

54. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ለቱሪዝም አገልግሎት ተቋማት ስለሚደረግ የማበረታቻ ሽልማት በሚመለከት የሽልማትና ማበረታቻ መመሪያ ረቂቅ የተዘጋጀ ሲሆን ይህን መመሪያ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጸድቆ ተግባራዊ እንደሚደረግ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

55. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሽልማትና ማበረታቻ መመሪያ ረቂቅ እንደተዘጋጀ ቢገለጽም በኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ረቂቅ መመሪያው ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

56. በቱሪዝም ሴክተር የተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ያሳዩ አካላት የሚበረታቱበትን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የተሻለ አገልግሎት ለደንበኞቻቸው የሚሰጡ እና ለሀገርም የሚጠበቅባቸውን የውጭ ምንዛሪ መጠን የሚያስገቡ ድርጅቶች እንዳይበረታቱ ያደርጋል፡፡

## 2.2 ለአስጎብኚ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ጥራት ያለው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በተመለከተ፤

### ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ የገቡ ተሽከርካሪዎች መረጃ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መያዙን በተመለከተ

57. አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት አገልግሎት እንዲውሉ ከቀረጥ ነጻ ያስገቡትን ተሽከርካሪዎችና ንብረቶች ሙሉ መረጃ (የተሽከርካሪ አይነት፣ እና የሰሌዳ ቁጥሮችን ጨምሮ) ሚኒስቴር መ/ቤቱ መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለአስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ የገቡ ተሽከርካሪዎች የተሟላ መረጃ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝግቦ አለመያዙን፣ የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚያስረዳ በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ለማስገባታቸው

ሳይረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እና ፈቃዳቸውም እንደሚታደስላቸው በናሙና ከታዩ የአስጎብኚ ድርጅቶች የግል ፋይል ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ መብትን በመጠቀም ያስገቡዋቸውን ተሽከሪካሪዎች መረጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚሰጣቸው የድጋፍ ደብዳቤ መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ስለሚደረግ መረጃዎቹ እንዳሉ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

60. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሟላ መረጃ ይያዛል ቢሉም በኦዲት ስራ ወቅት መረጃዎቹ ተጠይቀው የተሟላ መረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

61. በቀረጥ ነጻ ድጋፍ የገቡ ተሽከርካሪዎችና ንብረቶች መረጃ በተሟላ መልክ አለመያዙ መንግስት ለዘርፉ ያደረገውን የቀረጥ ነጻ ድጋፍ መጠን እንዳይታወቅ እና ለአስጎብኚ ድርጅቶች የተደረገው የቀረጥ ነጻ ድጋፍ መጠን የታለመለትን ዓላማ ስለማሳካቱ በትክክል ለማወቅ አያስችልም፡፡

## አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ንብረቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ለማስጎብኘት አገልግሎት ስለማዋላቸው

62. ማንኛውም አስጎብኚ ድርጅት እና ግለሰብ አስጎብኚ ከቀረጥ ነጻ ያገኘውን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለማስጎብኘት አገልግሎት ሥራ ብቻ ስለመዋሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

63. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስጎብኚ ድርጅት እና ግለሰብ አስጎብኚ ከቀረጥ ነጻ ያገኘውን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለማስጎብኘት አገልግሎት ሥራ ብቻ ስለመዋሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደረግ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

64. ስለጉዳዩ በናሙና የተጠየቁ የአስጎብኚ ድርጅቶች እና ማህበራቸው ተጠይቀው አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያስገቧቸውን ንብረቶች ወይም ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋል እንዳለባቸው ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/2003 ላይ የሚገልጽ ቢሆንም የታለመለት ዓላማ የሚለው ቃል ትክክለኛ ተግባራቶች አለመገለጹ ችግር ፈጥሮብናል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ተሽከርካሪዎቻቸውን ለሥራ ሲያሰማሩ የኢትዮጵያ የገቢዎችና

ጉምሩክ ባለሥልጣን ለታለመለት ዓላማ እያዋላችሁ አይደለም በማለት ተሽከርካሪዎቻቸውን እየያዘ ችግር እንደፈጠረባቸው እና የትኞቹ ተግባራት (activities) የተባለለት ዓላማ (የማስጎብኘት አገልግሎት) እንደሆኑ እና የትኞቹ ተግባራት ለታለመለት ዓላማ (የማስጎብኘት አገልግሎት) እንዳልሆኑ ባልተጠቀሰበት ሁኔታ እንደተረዳው እየተረጎመ መግባባት ላይ መድረስ አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

65. ስለሁኔታው የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የተባለለት ዓላማ ወይም የማስጎብኘት አገልግሎት ተግባራቶችን (activities) በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ስላልደረሳቸው የማስጎብኘት ስራውን በተረዱት ልክ ከቀረጥ ነጻ የገቡትን መኪኖች ቁጥጥር እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

66. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ለታለመለት ዓላማ በሚለው ፅንሰ ሀሳብ የህግ ትርጓሜ ላይ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስለጣን ጋር ምክክር እየተደረገ ሲሆን የታለመለት ዓላማ የሚለው አስጎብኚ ድርጅቶች ከውጭ ሀገር ቱሪስቶች በማስመጣት አገራችንን እንዲጎበኙ ለሀገርም የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ውይይቶች እንዳስረዱ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

67. አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኙትን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለታለመለት ዓላማ ማዋል እንዳለባቸው በመቀናጀትና በመግባባት የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ አገሪቱ ከዘርፉ አገኛለሁ ብላ በማበረታቻ መልክ የተወችውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ገቢ ዓላማውን እንዳይመታ የራሱን አሉታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## 2.3 የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶችን በሚመለከት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር፣ የመረጃ ልውውጥና አያያዝን ቀልጣፋ መሆኑን በተመለከተ፡፡

### የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት ስለመዘርጋቱና እንዲሻሻል ስለመደረጉ

68. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአለም አቀፍ ደረጃ ቱሪስቶችን ወደ አገሪቱ ለመሳብ እንዲረዳ አገሪቱ ያላትን የባህልና ቱሪዝም መስህቦች የሚመለከቱ መረጃዎችን ሊያሰባስብ ይገባል፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎችንም በማደራጀት የቱሪዝም የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ከሆኑት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት መዘርጋትና መረጃዎቹንም

በየጊዜው እንዲሻሻሉና ወቅታዊ ማድረግይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ወቅታዊ የሆኑ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት የማሰራጨት ሥራ መስራት አለበት፡፡

69. ይሁን እንጂ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ሥራ የተጀመረ ቢሆንም የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት አለመዘርጋቱ እና ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት አለመሰራጨቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በናሙና ለታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት ዘርግቶ የተቀላጠፈ መረጃ (የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን፣ አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች፣ ከቱሪዝም አንጻር የገበያው ፍላጎት፣ ወዘተ...) ለአስጎብኚ ድርጅቶች እንደማያደርስ የገለጹ ሲሆን፣ እንዲሁም የአስጎብኚ ድርጅቶቹም የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘና እና በየጊዜው ወቅታዊ ስለመደረጉና ተፈላጊውን መረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መላክ አለመላካቸውን እንደማይከታተል ገልጸዋል፡፡

70. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሚፈለገው ደረጃ የቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስራ የመስራት ክፍተት እንዳለ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

71. የአገሪቱ የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማዕከል ደረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት አለመዘርጋቱ እና መረጃዎቹን በመጠቀም ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ባለመድረሱና ባለመተዋወቁ ሀገሪቱ ያላትን የቱሪዝም መስህቦች በአግባቡ የማስተዋወቅ እና የማሳወቅ ስራ እንዳይሰራ የመረጃ እጥረት ክፍተት የሚፈጥር እና ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ያህል ጥቅም እንዳይገኝ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

### የቱሪዝም የገበያ ትስስር መፍጠርን በተመለከተ

72. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ገበያ የማስተዋወቅ ስራን ከሚያግዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነቱን በማጠናከርና ወቅታዊ የገበያ ጥናት ስራዎችን በቅንጅት በመስራት የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገፅታ በአለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት በማስተዋወቅ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር ሊፈጥር ይገባል፡፡

73. የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ያልተሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡ በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች እና አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የቱሪዝም ገበያ የማስተዋወቅ ስራን ከሚያግዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነቱን በማጠናከርና ወቅታዊ የገበያ ጥናት ስራዎችን በቅንጅት በመስራት የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገፅታ በአለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ በዋናነት የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት እንደተጠበቀው እንዳልተሰራ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሬጉላቶሪ አካል እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት የቱሪዝም የገበያ ማስፋፋት ስራ መስራቱን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

74. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂን በመጠቀም አስጎብኚ ድርጅት ገበያን በማፈላለግና የኢንፎርሜሽን ፍሰት ሥርዓት ዘርግቶ እየሰራ ሲሆን ይህንን ዌብ ሳይት እየተጠቀሙ ያሉ አስጎብኚ ድርጅቶች በርካታ መሆናቸውን በየጊዜው ከባለድርሻ አካሎቻችን ጋር በምናደርገው የሚክክር መድረክ ለመረዳት እንደቻሉና ለወደፊቱም ከዚህ በላይ መስራት እንደምጠበቅባቸው በመረዳት የስታቲስተክና መረጃ ጥንቅር ዳይሬክቶሬታችን እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የመረጃ ስርዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬታችን በጋራ እየሰሩ እንደሚገኙ በነባራዊ ሁኔታ ላይ የላቸውን አስተያየት ገልጿል፡፡

75. የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ባለመሰራቱ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በሚፈለገው መጠን እንዳያድጉ እንዲሁም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ መጠን ለማሳደግ እንዳትችል እንቅፋት ሆኗል፡፡

## አገሪቱ ያላትን የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁና እንዲለሙ መደረጉን በተመለከተ

76. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አገሪቱ ያላትን ሁሉንም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉላቸው በማድረግ አገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ መጠን ማግኘት እንድትችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

77. ይሁን እንጂ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አገሪቱ ያላትን ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ በአገሪቱ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቱሪስት መስህቦች ለቱሪዝም እና ለቱሪስቶች አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማቶች እንዳልተሟላላቸው አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው አስጎብኚ

ድርጅቶች፣ የአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በሰጡት መልስ አብዛኛዎቹ (ለምሳሌ፡ የሶፍ ዑመር ዋሻ፣ መልካ ቁንጡሬ፣ ወዘተ.) አገሪቱ ያላት የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረት ልማት አውታሮች እንዲሟሉላቸው በማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በቂ የገበያ ትስስር ስራ እንዳልተሰራ ገልጸዋል፡፡

78. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ደረጃውን የጠበቀ ገበያ እንዲፈጠር ለማስቻል ባለድርሻ አካላት ህጋዊ መሰረት ባለው ተቋማዊ አሰራር ተደራጅተው ያለው ክፍተት እንዲሞላ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና በቱሪዝም ቦርድ የሚመራ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት በመንግስት እንዲቋቋም መደረጉን ሥራው መጀመሩን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

79. አገሪቱ ያላትን ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ባለመደረጉ ሀገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል፡፡

## የማስጎብኘት አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መኖሩን በተመለከተ

80. በአገሪቱ ውስጥ ለቱሪስቶች የተቀላጠፈና ጥራት ያለው የማስጎብኘት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለስልጣን እና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ የማስጎብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

82. በናሙና የታዩ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች፣ የአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ የአዲስ አበባ መስተዳደር እና የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ ድጋፍ ከማድረግ፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ለተከሰቱት እና ሊከሰቱ ለሚችሉት ችግሮች መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

83. ስለጉዳዩ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ችግሩ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን በክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር በሚመራው የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ውስጥ የክልል እና የሁለቱ ከተማ መስተዳደር ኘሬዝዳንቶች፣ የሚኒስቴር መ/ቤቶች ሚኒስትሮች፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የኢንቨስትመንት ባለስልጣን እና ሌሎች አባል የሆኑበት ምክር ቤት በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሉ በሚባሉና ቱሪዝሙን የገጠሙ ችግሮችን በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

84. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ ተጠቀሰውን መልስ ቢሰጥም ከአስጎብኚ ድርጅቶች እና ከድርጅቶቹ ማህበር የተዘረዘሩ ችግሮችን በሙሉ ለትራንስፎረሜሽን ምክር ቤት መቅረብ የሌለበት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በራሱ ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለአብዛኛዎቹና ስትራቴጂካዊ ያልሆኑ ማነቆዎች መፍትሄ ያመጣ ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መስረጃዎች ተጠይቀው የልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

85. ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አለመኖሩ የማስጎብኘት አገልግት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች በአፋጣኝ ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት እንቅፋት ሆኗል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

86. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን  እንዲሁም የተዘረጋውን ሥርዓት ለመተግበር የሚካሄደው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል የአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ያልወጣ መሆኑ፣
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው አስጎብኚ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች  ትክክለኛቱ ሳያረጋግጥ መሆኑ፣
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው  ተሽከርካሪዎች በጎን እና በጎናቸው የሚለጥፉት  የየድርጅታቸው ዓርማ መጠን ስታንደርድ ያላወጣ እና መለጠፋቸውንም የማይከታተል መሆኑ፣
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚዎች መመሪያ /Minimum Standard Tour Operators Guide/ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ያላዘጋጀ እና ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣
- ❖ ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲያድስ የውጭ ምንዛሪ እንዲያንቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ስለማግኘታቸውና በየአመቱ ስለማሳደሳቸው እና በየዓመቱ ሪፖርት የሚያደርጉት የውጭ ምንዛሪ መጠን ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ❖ ከቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት የቅሬታና የአቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣  በሚኒስቴር መ/ቤቱ ደረጃ መፍታት ያልተቻሉትን ቅሬታዎች ከሚመለከታቸው የመንግስት እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ችግሩ እንዲፈታ ያላደረገ መሆኑ፣

- ❖ በማስጎብኘት ሥራ ለተሰማሩ ድርጅቶችና ባለሙያዎች በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት የማበረታቻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ❖ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ ያስገቡት ተሽከርካሪዎች የተሟላ መረጃ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፣ እንዲሁም የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚያስረዳ በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ለማስገባታቸው ሳይረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው እና ፈቃዳቸውም የሚታደስላቸው መሆኑ፣
- ❖ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋል አለመዋላቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት በመዘርጋት እና ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት የማያሰራጭ መሆኑ፣
- ❖ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ስለመሰራቱ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- ❖ ሀገሪቱ ያላት አብዛኛዎቹ የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባባር ያልተደረገ መሆኑ፣
- ❖ የቱሪስት ማስጎብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሄ ለማምጣት ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

87. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

88. የባህልና ቱሪዝም ሚኒቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅት በመፍጠር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-


- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል እንዲሁም ቱሪስቶች እንደፍላጎታቸው መገልገል እንዲችሉ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ሊያወጣና በወጣው ደረጃ መሰረት ድርጅቶቹን እየመዘነ ደረጃ ሊሰጥ እና በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚሰጥበት ወቅት የተቀመጠውን መስፈርት በጽሁፍ ማስረጃ የሚቀርበውን ሁሉ በአካል የሚያረጋግጥበት እና ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ ለማሳደስ የቀረቡት ባለሙያዎች፣ ግብአቶች እና ቁሳቁሶች በሙሉ መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ለማስጎብኘት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የየድርጅታቸውን ዓርማ በጎን እና በጎናቸው የሚለጥፉበት ሥርኣት ሊዘረጋና ተግባራዊነቱን ሊከታተል እንዲሁም የተሽከርካሪዎች ዓርማ መጠንን ስታንደርድ ሊያወጣ እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፣
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እንደ መነሻ የሚያገለግል የአስጎብኚ መመሪያ /Minimum Standard Tour Operators Guide/ ሊያዘጋጅ እና ይህንን መሰረት በማድረግ እና አስጎብኚ ድርጅቶቹም በራሳቸው አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ የውጭ ምንዛሪ እንዲያንቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ስለማግኘታቸው በየአመቱ ማሳደሳቸውን ሊያረጋግጥ እና በየዓመቱ ሪፖርት የሚያደርጉት የውጭ ምንዛሪ መጠን ትክክለኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- ከቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በቱሪዝም ሴክተር በተለይም በማስጎብኘት ሥራ ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙትን አካላት ዕውቅና የሚሰጥበት የማበረታቻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባዊ ሊደረግ ይገባል፣
- የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ ያስገቡትን ተሸከርካሪዎች የተሟላ መረጃ (የሻንሲና የሞተር ቁጥር፣ የሰሌዳ አይነት ሞዴል፣ መቼ የማበረታቻው ተጠቃሚ እንደሆነ እንደገባ ወዘተ...) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝግቦ ሊያዝ እንዲሁም ተሸከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ አስጎብኚ ድርጅቶች በየዓመቱ ፈቃዳቸውም ከመታደሱና የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት እንቅስቃሴያቸውን የሚያስረዳ በየዓመቱ በውጭ ምንዛሪም ሆነ በብር ገቢ ስለማስገባታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያገኟቸውን ተሽከርካሪዎች ለታለመላቸው ዓላማ ማዋላቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል ሊያደርግ እና ከተፈቀደላቸው ውጭ ሲጠቀሙ በተገኙት ላይ የዕርምት እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ የቀረጥ ነጻ መብት አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚነሱ የተለያዩ አለመግባባቶችን በፍጥነት የሚፈቱበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የማስጎብኘቱ አገልግሎት የተቀላጠፈ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃ ልውውጥና ፍሰት ስርዓት በመዘርጋት እና ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፣
- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥራ በስፋት ስለመሰራቱ የክትትልና ቁጥጥር ሰራ ሊሰራ ይገባል፣
- ሀገሪቱ ያላት ሁሉም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና የመሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት የጎብኚዎችን ቁጥር የሚያድጉበትን ሁኔታ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የቱሪስት ማስጎብኘት አገልግሎት ዘርፉን ለማሳደግ፣ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት እና ተጨባጭ መፍትሂ ለማምጣት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣

ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፣

89. በመጨረሻም ለባህልና ቱሪዝም ሚኒቴር፣ በኦዲት ወቅት የታዩት፣ ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት፣ ለቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣ እና በናሙና ተመርጠው ለታዩት የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 2፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እና የድርጅቶቹ አገልግሎት አሰጣጣቸው ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፡፡ | 1. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ሊያወጣላቸው ይገባል፡፡ |
| | 2. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአስጎብኚነት ለሚሰማሩ ባለሙያዎች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት አውጥቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3. የአስጎብኚዎች የሙያ ብቃት በየጊዜው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 4. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለአስጎብኚ ድርጅቶች የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ እና ሊታደስ ይገባል፡፡ |
| | 5. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር የአስጎብኚ ድርጅቶች የተሽከርካሪዎች ዓርማ ስታንደርድ ሊያወጣላቸው እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 6. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ማንኛውም የአስጎብኚ ድርጅት የአስጎብኚ መመሪያ ለማዘጋጀት እንደ መነሻ የሚያገለግል /minimum standard/ አዘጋጅቶ ለሁሉም ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 7. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ማንኛውም የአስጎብኚ ድርጅት ሚ/ር መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መነሻ /minimum standard/ መሰረት የራሳቸውን የአስጎብኚ መመሪያ /Tour Operators Guide/ አዘጋጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 8. አስጎብኚ ድርጅቶች ወርሃዊ የስራ አፈጻጸም እና በውጭ ምንዛሪ ያገኙትን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ሪፖርት በየወሩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 9. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ለአስጎብኚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ስሰጥ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያቀሳቅሱ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 10. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር በየደረጃው የሚገኙ የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር የተያያዘ አገልግሎት ለሚሰጡ ሠራተኞቹ አቅማቸው እንዲጎለብቱ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 11. ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር የክልል ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎችን ማብቃትና መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 12. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 13. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | በተያያዘ ለሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና የሚፈቱበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 14. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቱሪዝም ሴክተር ለተሰማሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የላቀ አገልግሎት ላሳዩ አካላት ማበረታቻ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 2. ለአስጎብኚ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ጥራት ያለው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን መገምገም፡፡ | 15. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ የማስፈጸም አቅም መገንባት አለበት፡፡ |
| | 16. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቱሪስት ማስጎብኘት አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማህበራትና ማሰልጠኛ ተቋማት የሚጠናከሩበትንና የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የዘርፉን የትምህርትና ሥልጠና አቅም ማጎልበት አለበት፡፡ |
| | 17. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቱሪስቶች ደህንነትና በጉብኝት ሥርዓት ዙሪያ የድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 18. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚዎች ለቱሪስቱ በቅድመ ጉብኝት፣ በጉብኝት ጊዜና ከጉብኝት በኋላ በየደረጃው የሚያገኛቸው የአገልግሎት ቅብብሎሽ ሥርዓት በማሻሻል፣ የተሳለጠና የተደራጀ አገልግሎትን እንዲሰጡ የአሠራር እና የግብረመልስ/ Feedback/ ስርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊነታቸውን መከታተል አለበት፡፡ |
| | 19. ማንኛውም አስጎብኚ ድርጅት እና ግለስብ አስጎብኚ ከቀረጥ ነጻ ያገኘውን ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለማስጎብኘት አገልግሎት ሥራ ብቻ ስለመዋሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20. ለአስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ የገቡትን ተሽከርካሪዎችና ንብረቶች መረጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| 3. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች በተመለከተ ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር፣ የመረጃ ልውውጥና | 21. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት የተጠናከረ የቱሪዝም መረጃና ኢንፎርሜሽን ልውውጥና ፍሰት ስርዓት መዘርጋትና በየጊዜው እንዲሻሻል ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 22. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| አያያዝን ቀልጣፋ መሆኑን መገምገም፡፡ | አካላት ጋር ወቅታዊ የፕሮሞሽናል ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት የማሰራጨት ሥራ መስራት አለበት፡፡ |
| | 23. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ገበያ የማስተዋወቅ ስራን ከሚያግዙ ባለድርሻ አካላት ጋር (Public-Private partnership) ግንኙነቱን በማጠናከርና ወቅታዊ የገበያ ጥናት ስራዎችን በቅንጅት በመስራት የአገሪቱ የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገፅታ በአለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት በማስተዋወቅ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር ሊፈጥር ይገባል፡፡ |
| | 24. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አገሪቱ ያላትን ሁሉንም የቱሪዝም መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ በማድረግ አስጎብኚ ድርጅቶች ከዘርፉ የሚጠበቅባቸውን የውጭ ምንዛሪ መጠን ማስገባት እንዲችሉ የሚደረግበትን አግባብ ማመቻቸት አለበት፡፡ |
| | 25. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከዓለም ሀገራት ጋር ጠንካራ የቱሪዝም የኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲ በመስራት ቀጣይነት ያለው የቱርዝም ገበያ /Sustainable Tourism Marketing/ የማስፋፋትና ነባሩን ገበያ የማቆየት ስራ በመስራት የአስጎብኚ ድርጅቶችን የገበያ ፍላጎት ማቃለል ይጠበቅበታል፡፡ |
| | 26. ማንኛውም የአስጎብኚ ድርጅት ወይም ግለሰብ አስጎብኚ የተሰጠውን ወይም የታደሰውን የሙያ ብቃት ፎቶ ኮፒ በተቋሙ ውስጥ በሚታዩ ስፍራ የመስቀል ወይም እየተንቀሳቀሰ ለሚሠራቸው ስራዎችም በስራው ወቅት ይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡ |
| | 27. አስጎብኚ ድርጅቶች ተገቢ ብሮሸሮችን በማሳተም፣ በኢንተርኔት ድህረ-ገጽ በማዘጋጀት፣ በሀገርም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ተደራሽ እና ተደማጭ የሆኑ የተለያዩ መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም የሚሰሩበትን የቱሪዝም ዘርፎችና መዳረሻዎችን እንዲሁም ድርጅቶቻቸውን ሊያስተዋውቁ ይገባል፡፡ |
| | 28. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የአስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከኢንቨስትመንት ባለስልጣን እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |

# አባሪ 3፡ በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው እና ማስረጃ የተሰበሰበባቸው ባለድርሻ አካላትና የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ዝርዝር

**፩. በናሙና የተመረጡ ለባለድርሻ አካላት**

1. ኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት፣
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣
3. አዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣
4. ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣
5. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማህበር፣

**፪. በናሙና ለተመረጡ አስጎብኚ ድርጅቶች**

1. ኢትዮ ናሽናል አስጎብኚና ጉዞ /Ethionational Tour and Travel/
2. ኤም ዲ አስጎብኚ ድርጅት /MD Tour Services/
3. አቮላ አስጎብኚ ድርጅት
4. ሰንራይዝ አስጎብኚና ጉዞ /Sunrise Travel and Tour/
5. አፍሮ ግሎባል አስጎብኚ /Afro Global Tour/
6. ቤጋ የማስጎብኘት አገልግሎት /Bega Tour Services/
7. ክብራን ብዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /Kibran Buissness Plc/
8. ያማ ኢትዮጵያ አስጎብኚና ጉዞ /Yama Ethiopia Tours PLc/
9. ሰርቲን ሰንስ አስጎብኚ /13 Suns Tour/
10. ሃፒ ሂቬን አስጎብኚ /Happy Heaven Tours/
11. ጃምቦ አስጎብኚ እና የጉዞ ወኪል /Jambo Tour and Travel Agency/
12. ቴራ ኢንኮጊታ አስጎብኚ /Tera Incogita/
13. ኤክስፐሪያንስ ኢትዮጵያ ተራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር /Experience Ethiopia Travel Plc/
14. ጋላክስ ኤክስፐሬስ ስርቪስስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር / Galaxy Express Services PLc/
15. ብሔራዊ አስጎብኚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /National Tour Plc/